ደ/ሰ/መ/ኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ/ሰ/ት/ቤ/ት/ክ

# (ከፍጥረት እስከ ራእይ)

«እርሱም፥- የሰው ልጅ ሆይ፥ ያገኘኸውን ብላ፤
ይህን መጽሐፍ ብላ...አለኝ።
አፌንም ከፈትሁ መጽሐፉንም አጎረሰኝ።
እርሱም የሰው ልጅ ሆይ፥ አፍህ ይብላ
በምሰጥህም በዚህ መጽሐፍ ሆድህን ሙላ አለኝ።
እኔም በላሁት፥ በአፌም ውስጥ እንደ ማር ጣፈጠ።»

ትንቢተ ሕዝ. ፫፥፩-፫

በዓለም በከፍተኛ ሁኔታ የተነበበና እየተነበበ ያለ መጽሐፍ እስከ ዛሬ ድረስ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። በእምነት ውስጥ ያለ ሃይማኖትን ሊያውቅበት ፤ ማንነቱን ሊመለከትበት ፤ የእግዚአብሔርን ነገር ሊማርበት ፤ በሥርዓት ሊጓዝበት ፤መንግሥተ ሰማያትን ሊወርስበት ሲያነበው በእምነት ውስጥ የሌለ ደግሞ «ምን ይላል ? ምንስ መልእክት አለው?» በማለት ብቻ እና የፍልስፍናን መጽሐፍ አንብቦ ለመከራከሪያ እንዲመቸው ሲል ያነበዋል። ከዚህ ውጭም ከክርስትናው እምነት ውጪ ያሉ ለግንዛቤ እና «አንብቤዋለሁ» ለማለት ብቻ በማንበብ ይጠቀሙበታል። አንዳንዶችም ለትችት።

ሆኖም ግን ከዚህ በታች የተጻፈው ግጥም መጽሐፍ ቅዱስን መመሪያው አድርጎ ለሚኖረው ሕዝብ ማስታወሻ እንዲሆነውና የእያንዳንዱን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል መጠሪያ የሆነውን ርእስ በቀላሉ እንዲያውቀው ፤ ማንስ የትኛውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እንደጻፈ ለማሳወቅ ሲሆን በተለይም የኢትዮጲያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የምትጠቀምበት በተለምዶ ሰማንያ አሐዱ በመባል የሚታወቀው መጽሐፍ ቅዱስ ከእዝራ ሱቱኤል እስከ መጽሐፈ ሄኖክ ድረስ ያለውን አንባብያን በሚገባ እንዲያነቡትና ፍሬ እንዲያፈሩበት ለማበረታታት ጭምር ፤ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥም ለሚነሱ አንዳንድ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት እና ግንዛቤን ለማስጨበጥ እንዲረዳም ታስቦ ነው።

«ስድሳ ስድስቱ» በመባል የሚታወቀው መጽሐፍ ቅዱስ «ሰማንያ አሐዱ» ተብሎ በሚታወቀው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉትን በሙሉ አካትቶ ስላልያዘ አንባብያን ሰማንያ አሐዱ የተሰኘውን መጽሐፍ ቅዱስ በማንበብ ሃይማኖትን ገንዘብ እንዲያደርጉ ፤ የብዙ ጥያቄዎችንም መልስ እንዲያገኙበት ለማበረታታት ነው። በሥነ - ግጥሙ ላይ የተሰመረባቸው በሙሉ ከመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ውስጥ የእያንዳንዳቸው መጠሪያ ነው። በቀን የተወሰኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን ማንበብ በዓመት ውስጥ መጽሐፍ ቅዱስን አንብቦ ለመጨረስ ያስችላል። በውስጡ የተጻፈውን ዐውቆ ሰማያዊ ምስጢርን ተረድቶ ሕይወትን ለመቀየር ደግሞ የእያንዳንዱ አንባቢ ጥያቄና መልስ ነው።

ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ በመልእክቱ በእናንተ ስላለ ተስፋ ምክንያትን ለሚጠይቁአችሁ ሁሉ መልስ ለመስጠት ዘወትር የተዘጋጃችሁ ሁኑ (፩ጴጥ. ፫፥፲፭) ብሎ ያስተማረበት አንቀጹ መልስ ለመስጠት የግድ መጽሐፍ ቅዱስን መረዳት እንደሚኖርብን ለማስገንዘብ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የምስጢር መክፈቻ የእንቆቅልሽ መፍቻ መሣሪያ ነውና።

# ብሉይ ኪዳን

ዘፍጥረት ዘጸአት ዘሌዋውያን፥
ዘኍልቊ ዘዳግም ከብሉይ ኪዳን፥
አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ሲፈቅዱሥላሴ፥
በነብየ እግዚአብሔር ተጻፉ በሙሴ።

በሙሴ እግር ገብቶ ሕዝቡን ባሳለፈ፥
መጽሐፈ ኢያሱ በኢያሱ ተጻፈ።

መጽሐፈ መሳፍንት መጽሐፈ ሩት፥
መጽሐፈ ሳሙኤል አንድና ሁለት፥
ያስረዳል ታሪኩ የሶምሶንን ዝና፥
የሳዖል የዳዊት በእስራኤል ንግሥና

መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ ካልዕ፥
መጽሐፈ ዜና ቀዳማዊ ካልዕ፥
የንጉሥ ሰሎሞን የነብይ ኤልያስ፥
የነገሥታት ታሪክ ነገረ ሕዝቅያስ፥
ተዘግቦበታል የአክአብ ውድቀት ዜና፥
በከንቱ እንደቀረ የሳዖል ንግሥና።

የእስራኤልን ነገር የኢየሩሳሌምን፥
በመጽሐፈ ዕዝራ ካህኑ ጻፈልን።

ቅጽርዋ ፈርሷል የሚል መልእክት
የደረሰው፥
ስለ ኢየሩሳሌም እጅጉን ያዘነው፥
የንጉሥ አገልጋይ ታላቅ የጸሎት ሰው፥
መጽሐፈ ነህምያን ነህምያ ጻፈው።
ንጉሥ ፊት ለመቆም ንጉሥ አከበራት፥
እግዚአብሔር አስቴርን ግርማ ሞገስ ሆናት
ንጉሥ የመረጣት ንጉሥ ያነገሣት፥
በመጽሐፈ አስቴር ታሪክ ተጻፈላት።

ያጣ ተስፋ እንዳይቆርጥ ያዘነን ያጽናናል
መጽሐፈ ኢዮብ ትዕግሥት ያስተምራል

«እንደ ልቤ» ብሎ ጌታ ስም የሰጠው
መዝሙረ ዳዊትን ቅዱስ ዳዊት ጻፈው

መጽሐፈ ምሳሌ መጽሐፈ መክብብ፥
መኃልየ መኀልይ የሰሎሞን መዝሙር፥
፫ቱን መጻሕፍታት ጻፋቸው ሰሎሞን፥
እግዚአብሔር የታየው በምድረ ገባዖን።

ስለ አምላክ መወለድ ስለ ድንግል መጽነስ
ስለ አምላክ ክርስቶስ በምድር መመላለስ
ግልጽ ትንቢቶችን አብዝቶ የጻፈው፥
ትንቢተ ኢሳይያስ ብዙ መልእክት አለው

ትንቢተ ኤርምያስ ድንቅ ቃል ያለበት፥
ስለ እስራኤል ልጆች በደል ተጻፈበት፥



የኢየሩሳሌም መከበብ በጠላት፥
የካህናት መገደል የእናት ልጇን መብላት

የነበረውን ግፍ የታየውን ጥፋት፥
ሰቆቃው ኤርምያስ ገልጾታል በብዛት።

ትንቢተ ሕዝቅኤል ትንቢተ ዳንኤል፥
ትንቢተ ሆሴዕ ትንቢተ አሞጽ ትንቢተ
ኢዩኤል፥
ስለ አይሁድ ኃጢአት ስለ መርገም ዕጣ፥
ስለ ሕግ መፍረስ ስለ እግዚአብሔር ቁጣ
የጾም ጸሎት አዋጅ የፈተና ጽናት፥
በረቂቅ ተጽፏል ከአሣት መኻል መውጣት

ትንቢተ አብድዩ ትንቢተ ዮናስ፥
ሰባት ምዕራፍ ያሉት ትንቢተ ሚክያስ፥
ትንቢተ ናሆም ትንቢተ ዕንባቆም
ትንቢተ ሶፎንያስ ፣
ትንቢተ ሐጌ ትንቢተ ዘካርያስ
ትንቢተ ሚልክያስ ፣
ዘጠኙ መጻሕፍት ታሪክ ሐሳባቸው፣
ስለ አይሁድ መሳሳት ስለ ጥፋታቸው፣
ስለ እግዚአብሔር ቅጣት ስለ ቤቱ አድሳት
ስለ አይሁድ መመለስ ስለ
እግዚአብሔር አሥራት ፣
ትልቅ ታላቅ መልእክት አለ በውስጣቸው፣
የእግዚአብሔር ተአምራት ስለታየባቸው

የብሉይ ኪዳን መጻሕፍተ ቀኖና፥
ዝርዝር ስያሜያቸው ተጽፈዋልና።
እነሆ ስማቸው በግልጽ ይነበቡ፥
ስለታየባቸው የእግዚአብሔር ጥበቡ።

በአሳብ ሲነጋገር ከእግዚአብሔር በብርቱ
መልአክ ተገልጾለት ኡርኤል ከፊቱ፣
ሁሉንም ጠይቆ ሁሉም መልስ አግኝቶ
ምሥጢር ተገልጾለት በመንፈስ ተሞልቶ
እዝራ አስፍቶ ጻፈ ገልጾለት ኡርኤል፣
መጽሐፈ እዝራ ካልዕ ወሱቱኤል።

ሁሉን ያስረዳሉ የእግዚአብሔርን ነገር
በእውቀት በጥበብ ሰው እንዲነጋገር።
መጽሐፈ ጦቢት መጽሐፈ ዮዲት፣
የሰውን አክብሮት ቆመው ከጌታ ፊት፣
መመስከራቸውን በግልጽ ያስተምራል፣
የሥላሴን ነገር በምሥጢር ያስረዳል።

መጽሐፈ መቃብያን ቀዳማዊ ካልእና ሳልስ
በሦስቱም መልእክታት መንፈስን የሚያድስ

የፍጥረትን ነገር አምልቶና አስፍቶ፣
ሁሉን ለሚችለው ለአምላክ ክብር ሰጥቶ
ለጣዖት አምላኪ ሕግ አልባ ለሆኑት፣
የእግዚአብሔርን ክብር ገና ሳልተረዱት
ተመለሱ እያለ መልእክት መንገሩን፣
ያስረዳል ጽሑፉ ትንሣኤና ሞቱን።

መጽሐፈ ሲራክ ምክር አዘል መልእክቱን፣
ጥበብ ከእግዚአብሔር ዘንድ
ከአምላክ መገኘቱን፣
ምን ያህል እንደሆን የሃይማኖት ክብር
ያስረዳል ትምህርቱ የእግዚአብሔርን ፍቅር

ጸሎተ ምናሴ ፣ ተረፈ ኤርምያስ
መጽሐፈ ሶስና፣
ጸሎትን ንስሃን እውቀትን ጨምረው
ይናገራሉና፣
ጠንቅቀን እንድናውቅ ሁሉንም በተርታ
ስለኛ ተጽፏል ምሥጢሩ የጌታ

መጽሐፈ ባሮክ፣ መጽሐፈ ጥበብ፣
ተረፈ ዳንኤል፣
አምላክን ማመስገን ጥበብን መረዳት
እንደ እዝራ ሱቱኤል፣
ተጽፎባቸዋል መወጣት እምነትን፣
በአምላክ የታመነ ከሞት እንደሚድን።

ስለ ሥነ ፍጥረት ስለ አዳም ልጆች ዘር
ሁሉንም በይፋ ዘርዝሮ የሚናገር፣
የአዳም የሔዋንን የቃኤል የአቤልን፣
አምላካዊ ሕግን ሥርዓተ እግዚአብሔርን
ጠንቅቆ የያዘ ሕግ የሚያስተምረው
መጽሐፈ ኩፋሌ ታላቅ ምሥጢር አለው

ስለ መንፈስ ቅዱስ ስለ መላእክቱ፣
ስለ እግዚአብሔር ፍጥረት ስለ ከዋክብቱ
ደግሞም ስለ ዘመን ስለ አቆጣጠሩ፣
መጽሐፈ ሄኖክ ያስረዳል ምሥጢሩ።

## ሐዲስ ኪዳን

አራቱ ወንጌላት ኪዳነ ሐዲስ፣
ማቴዎስ ማርቆስ ሉቃስ ዮሐንስ፣
የጌታን መወለድ ታላቅ የምሥራች፣
ብዕራቸው ጻፈች አፋቸው አወራች።

የሐይማኖት ነገር በግልጽ እንዲያበራ፣
በሉቃስ ተጻፈ የሐዋርያት ሥራ።

ደ/ሰ/መ/ኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ/ሰ/ት/ቤ/ት/ክ

ጌታ የመረጠው ጳውሎስ አስተማረ፣
ወደ ሮሜ ሰዎች መልእክቱን ጀመረ።

ሁለት መልእክታት ለሕዝበ ቆሮንቶስ፥
ጽፎ አስተማራቸው ሐዋርያው ጳውሎስ

መልእክት አዳረሰ ጳውሎስ ሐዋርያ፣
ስለ ጌታ ጻፈ ወደ ገላትያ።

ለኤፌሶን ሰዎች ለፊልጵስዮስ፣
እምነት ሐይማኖትን አስተማረ ጳውሎስ

ወንጌል ተሰበከ መንፈስን የሚያድስ፣
በጌታ ሐዋርያ ለሕዝበ ቆላስይስ።

የክርስቶስ ባሪያ ገባሪ ተአምራት፣
ለተሰሎንቄ ሕዝብ ሁለት መልእክታት፣
ጽፎ ላከላቸው የትጋትን ነገር፣
በእምነታቸው መኻል ስላለው መጠንከር

ወደ መንፈስ ልጁ ወደ ጢሞቴዎስ፣
ሁለት መልእክታት ጽፎ ላከ ጳውሎስ።
ወደ ቲቶ ሰዎች ደግሞም ለፊልሞና፣
ወደ ዕብራውያን መልእክቱን ጻፈና፣
ብሉይን ከሐዲስ ጋር እያመሳከረ፣
በ፲፬ መልእክታት ዓለም አስተማረ።

መልእክታት ተጻፈ ዓለምን የሚያድስ፣
ሁለቱ በጴጥሮስ ሦስቱ በዮሐንስ።

መሠረተ ሐይማኖት አዕማደ ምሥጢራት
ተጽፈው ተገኙ በጴጥሮስ መልእክታት።
ስለ ፍቅር ነገር ጥልቅ ምሥጢር አለው
በሦስቱ መልእክታት ዮሐንስ በጻፈው።
የያዕቆብ መልእክት የይሁዳ መልእክት
የዮሐንስ ራዕይ ምሥጢርና ትንቢት፣
ዘላለም የሚኖር ሕያው ቃል አላቸው፣
እስትንፋሰ እግዚአብሔር ስላረፈባቸው

ወስብሐት ለእግዚአብሔር!
አብርሃም ሰሎሞን

የሚያባራ ዝናብ መታን ከሚለው መጽሐፍ
የተወሰደ

abraham.solomon@yahoo.com